ተጓዦቹ

ከጠቢባን ምድር

👣👣👣ተጓዦቹ👣👣👣

🍂መንገደኛው ወንድሜ ሆይ ለጉዞ የሚያስፈልጉ ነገሮችን አዘጋጅተሀልን?
የተቅዋን ልብስ አዘጋጅተሀልን?አሏህን የመፍራት ልብስ !! ወይንስ ከሰማያት እና ከምድር ጌታ የሚያርቀውን የስሜት ካባን ነው የደረብከው!??
ለዚያች ጨለማና ጠባብ ጉድጓድ ስንቅ ሰንቀሀልን??መመለሻህ ወደ አርሷ መሆኑንን ዘነጋሀውን??
ከፅልመቷና ከጥበቷ ራስህን ለማዳን ጥረት አድርገሀልን⁉️

ጭንቀትና ሀሳብህን በሙሉ ለዚያች ለሩቅ እና ረዥሟ ሀገር አውለው፤በጀርባህ ተጋድመህ ትከሻዎች ሲሸከሙህ ምን ትል ይሆን❓
ድምፅህ በጨሀት እና በዋይታ የተቀላቀለ ሆኖ••<<ዋላቹህ ወዴት ትውስዱኛላቹ>>••ትል ይሆን!? ወይስ ••<<በቶሎ ውሰዱኝ ውሰዱኝ>>•• ይሆን ጥሪህ!?
እቀብር ላይ ምትሰጠውን ምላሽስ አስበሀዋል!?
አሏህ ሱ.ወ እንዲህ ይለናል፤

🌹 يُثَبِّتُ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ بِٱلْقَوْلِ ٱلثَّابِتِ فِى ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا وَفِى ٱلْـَٔاخِرَةِ ۖ وَيُضِلُّ ٱللَّهُ ٱلظَّٰلِمِينَ ۚ وَيَفْعَلُ ٱللَّهُ مَا يَشَآءُ
አላህ እነዚያን ያመኑትን በቅርቢቱም ሕይወት በመጨረሻይቱም (በመቃብር) በተረጋገጠው ቃል ላይ ያረጋቸዋል። ከሓዲዎችንም አላህ ያሳስታቸዋል። አላህም የሚሻውን ይሠራል።>>••

ወይስ ሀሳብህና ጭንቀትህ የተወገዙ ነገሮችን ለመመልከት ዘፈንን ለማዳመጥ፣አፍላሞችን ለመመልከት ፣እና የነፍስያህ ተገዥ ሆኖ ለመኖር ነው??

መንገደኛው ወንድሜ ተጓዦ እህቴ፦
      ተቅዋን ያነገበ እንደሆን በርግጥ ዳነ ፤በወንጀል የተሰነከረ በእርግጥ መክሰርን ከሰረ ፤የሰይጣንንም ጎራ የተከተለም ሰው ከእደለ ቢሶች ተርታ ምናጥ ሆነ።
የጌታውን ውዴታ ያሻም የፍላጎቱን ያገኛል
አሏህ ሱ.ወ እንዲህ ይለናል፤

🌹 أَلَآ إِنَّ أَوْلِيَآءَ ٱللَّهِ لَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ
ንቁ! የአላህ ወዳጆች በእነሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነሱም አያዝኑም።

እናማ ውዶቼ የጉዞ ሻንጣችንን በኽይራቶች ሞልተን ጠቃሚ ስንቆችን እንሰንቅበታ!!!
መመለሻችንን ወዴት ይሆን? እሚለውን በቀጣዩ ፌርማታ እንቃኘዋለን፤

ቢአውኒላህ🙏

👣👣ተጓዦቹ👣👣

••<የጉዞው ፍፃሜ የት ይሆን?>••

🍂ሀቢቢ ሁሌም ሊያሳስብህና መልስ ልታገኝለት የሚገባን ጥያቄ ልወርውርልህ፡
ራስህን በግልፅነት እና በማስተዋል ጠይቅ፤ አባቶችህና አያቶችህ የት አሉ!!? የቅርብ ወዳጆችህ የትስ ናቸው??
መልሱ ከሀዘንና ከእንባ ጋር ተቀላቅሎ ልቦችም በናፍቆት ተቃጥሎ እንዲህ ይላሉ••<...እነርሱማ መሬት ስር አፈርን ለብሰው ተጋድመዋል..!!>••
እውንም ይህ ነው መመለሻው
ይህ ነው መጨረሻው...
ወንድሜ ሆይ ...አሏህ ዘንድ ባለው መዝገብህ ውስጥ ወንጀሎችና ሀጢያቶችህ ተመዝግበውልሀል!!!
በስራህም ላይ ስንት ዝንጋቴ እና ግድፈቶች አሉ..
የታሪክ መዛግብ እንዳሰፈሩት ከእለታት በአንዱ ቀን ኢብራሂም ኢብን አድሀም ዘንድ ይመጣና እንዲህ ሲል ይጠይቀዋል ህንፃዎችህ የት አሉ??
ኢብራሂምም እጁን በመያዝ ወደ መካነ መቃብር ይወስዱትና እዚህ ናቸው!!ብለው ይመልሱለታል.

ስሚኝማ ውዴ እህቴ ....ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሠው አንድን ሬሳ ለመቅበር በተማሰ ጉድጓድ ውስጥ ቆሞ ሳለ ከብዙ አመታት በፊት የሞተችን የአንዲትን ሴት ፀጉር ይመለከታል
ከህሊናውም ጋር መሞገት ጀመረ፤ይህች ሴት ዞማ ፀጉሯን እንዴት ስትንከባከበው ውበትና ልስላሴውን እንዳያጣ ስትጠብቀው ኖራ ይሆን!??
ግና ይሄው ፀጉር ከአፈር ጋር ተለውሶ ምን እንደሚመስል ተመልከቺ!!

እናም እህቴዋ ዛሬ ነገ ሳትይ ጥርት ባለ ንሰሀ ወደ ጌታሽ ተዋደቂ፤
አሏህ ሱ.ወ እንዲህ ይለናል

🌹وَلَيۡسَتِ ٱلتَّوۡبَةُ لِلَّذِينَ يَعۡمَلُونَ ٱلسَّيِّـَٔاتِ حَتَّىٰٓ إِذَا حَضَرَ أَحَدَهُمُ ٱلۡمَوۡتُ قَالَ إِنِّى تُبۡتُ ٱلۡـَٰٔنَ وَلَا ٱلَّذِينَ يَمُوتُونَ وَهُمۡ كُفَّارٌۚ أُوْلَٰٓئِكَ أَعۡتَدۡنَا لَهُمۡ عَذَابًا أَلِيمًا
ጸጸትንም መቀበል ለእነዚያ ጎጢአቶችን ለሚሠሩ አንዳቸውንም ሞት በመጣበት ጊዜ «እኔ አሁን ተጸጸትኩ» ለሚልና ለነዚያም እነርሱ ከሓዲዎች ኾነው ለሚሞቱ አይደለችም:: እነዚያ ለእነሱ አሳማሚን ቅጣት አዘጋጅተናል::>>••

የጉዞውም እለት ከደረሰ መሸሻም ሆነ ማምለጫ አይኖረንም‼️

👣👣ተጓዦቹ👣👣

••<<ጉዞው ደረሰ!!>>••

🖤ውዱ ውንድሜ፡-
የምድራዊው ዐለም ፀጋ ምን ቢሰፋ ጊዜያዊ ነው::ምንም ቢገዝፍ ወራዳ ነው፤ለሊቱም ቢረዝም በጎህ መሸፈኑ አይቀሬ ነው::የዕድሜ እርዝማንም የሞትን ፅዋ ከመጎንጨት አያስጥለንም!!

🍂በዚህች ቅርቢቱ ህይወት ታላቋ እውነት ሞት መሆኗን አውቀሀልን? ክብሩ የላቀው ልቅናው የገነነው ጌታ አሏሁ ተባረከ ወተዐላ በቁርአኑ እንዲህ ይለናል፦

🌹وَجَآءَتۡ سَكۡرَةُ ٱلۡمَوۡتِ بِٱلۡحَقِّۖ ذَٰلِكَ مَا كُنتَ مِنۡهُ تَحِيدُ
የሞትም መከራ እውነቱን ነገር ታመጣለች። (ሰው ሆይ)፦ «ይህ ያ ከርሱ ትሸሸው የነበርከው ነው» (ይባላል)።🌌

ህመም ቢነካህ ወደ ሀኪም ትሸሻለህ ብትራብም ወደ ምግብ ፣ቢጠማህ ጥምህን ለመቁረጥ ውሀን ፍለጋ ትሯሯጣለህ
ሞት የመጥህ ለታ ወዴትስ ትሸሻለህ‼️

አሏህም በሌላ የቁርዐን አንቀፅ እንዲህ ይለናል

كَلَّآ إِذَا بَلَغَتِ ٱلتَّرَاقِيَ🌺
ንቁ (ነፍስ) ብሪዎችን በደረሰች ጊዜ፤
وَقِيلَ مَنۡۜ رَاقٖ🌺
«አሻሪው ማነው?» በተባለም ጊዜ።
وَظَنَّ أَنَّهُ ٱلۡفِرَاقُ🌺
(ሕመምተኛው) እርሱ (የሰፈረበት ነገር ከዚህ ዓለም) መልለየት መኾኑን ባረጋገጠም ጊዜ።

አዎን ❕ በማንኛውም ጊዜና በሁሉም ቦታ ላሉ መስማት ለሚችሉ ጆሮዎች መገንዘብና ማስተንተን ለሚችሉ ተልብ ባለቤቶች ጌትነትም ሆነ ዘውታሪነት ለዚያ ሁሌም ህያው ለሆነው እና ለማይሞተው አሏህ ቢሆን እንጂ ለማንም እንደማይገባ የምትበይን ሀቅ ነች!!
ምንም እንኳ ክብርና ሞገስ ቢኖረውም ዝናውቢገንም የሰው ልጅ ፍፃሜ ሞት ነው።ሁሉም ይጓዛል መሪውም ተመሪውም ሀብታም ደሀውም በብል ተበልቶ በሚያልቅ ነጭ ቁራጭ አቡጀዲ ተገንዞ!!ብርሀን በማይገባው ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ አፈሩን ተንተርሶ!!!
🎈የጉዞው ፍፃሜ ይሄ ቢሆን ጥሩ ግና ቀጥሎ ለሚከተለው የመቀስቀስ እና ረበል አለሚን ዘንድ የመጠየቅ ጉዞ መነሻ ነው።
ውዷ እህቴ አማኝ ወንድሜ ከበርዘሁ(ቀብሩ)ህይወት ቡሃላ ምን ይጠብቀን ይሆን!!??

👣👣 ተጓዦቹ 👣👣

፤ታላቋ ፈተና፤

🎈ውዱ ወንድሜ...ውጤታቸው ጀነት ወይም ጀሀነም የሆኑትን የታላቁ ፈተና ጥያቄዎችን አስታውሳቸው!!
።ኢማም አህመድ ሙስነዳቸው ላይ በዘገቡት ሀዲስ እንደተገለፀው ቀብሩ ውስጥ የሚከተሉት ጥያቄዎች ጠብቁናል
.ጌታህ ማን ነው??
ሀይማኖትህ ምንድን ነው?
ነብይህስ ማን ነው??
በእነኚህ የቀብር ጥያቄ ብቻ ጥያቄዎቹ አያቆሙም።
የትንሳኤ እለት እያንዳንዱ ሰው የማይቀሩለት ጥያቄዎች አሉ፦
እድሜህን በምን ጨረስከው ?
ወጣትነትህን በምን አሳለፍከው !??

ገንዘብህንስ ከምን ሰበሰብከው በምንስ ላይ ዐዋልከው!??
እውቀትህንስ ምን ሰራህበት!??

የልቅናው ባለቤት እንዲህም አለ፦

وَلَا تَقْفُ مَا لَيْسَ لَكَ بِهِۦ عِلْمٌ ۚ إِنَّ ٱلسَّمْعَ وَٱلْبَصَرَ وَٱلْفُؤَادَ كُلُّ أُوْلَٰٓئِكَ كَانَ عَنْهُ مَسْـُٔولًا
ለአንተም በርሱ ዕውቀት የሌለህን ነገር አትከተል። መስሚያ፣ ማያም፣ ልብም እነዚህ ሁሉ (ባለቤታቸው) ከእነሱ ተጠያቂ ነውና።
فَوَرَبِّكَ لَنَسْـَٔلَنَّهُمْ أَجْمَعِينَ
በጌታህም እንምላለን። ሁላቸውንም እንጠይቃቸዋለን፤

ለነዚህ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ለመመለስ የሚረዱት ትክክለኛ እምነት፤በጎ ስራ አሏህን በመፍራትና ፅናት፣ጥርት ያለ ንሰሀና ከወንጀሎች መጥራት መሆኑን መገንዘብ ልብ ብሏ።

ከመርመርህ በፊት እራስህን መርምረሀልን??
ከጥያቄው ለጥቆ እሚጠብቅህንስ አውቀሀልን??

ሲራጥ‼️
ኢብኑ ጀሪር ከአብዱሏህ አንስቶ እንዲህ ሲል ዘግቦዋል፦
ሲራጥ በጀሀነም ላይ የተረጋ እንደ ሰይፍ የሰላ ሲሆን የመጀመሪያው ጭፍራ እንደ መብረቅ፣ሁለተኛው እንደ ነፋስ ፣ ሦስተኛው እንደ ፈረስ ፣ አራተኛው በእንስሳት ፍጥነት ያልፋሉ፤መላኢኮችም ጌታችን ሆይ አድን (ሰላምን አስፍን) ይላሉ።
በሌላም ሀዲስ ሀቢባችን ሲራጥ ላይ በመሆን ኡመቲ ኡመቲ እያሉ ይማፀናሉ።
መንፋቀቅን እንጂ መራመድ ያቃተው ሰውም እስኪመጣ ድረስ።
እንዲህም አሉ፦በሲራጡ ዳርናዳር ላይ የታዘዙትን ሰው የሚይዙ ቆንጥሮች አሉ፤ተቧጭሮ የሚድን አለ፣ወደ ጀሀነምም ተቦጭቆ እሚውርድም አለ።
ሢራጡ በጀሀነም ጀርባ ላይ የተዘረጋ ሲሆን ሁላችንም በላዩ ላይ እንሄዳለን ጀሀነምንም ስትቀጣጠል እውነተኛ መመልከትን እንመለከታለን!!!

وَإِن مِّنكُمْ إِلَّا وَارِدُهَا ۚ كَانَ عَلَىٰ رَبِّكَ حَتْمًا مَّقْضِيًّا
ከእናንተም ወደ እርሷ ወራጅ እንጂ አንድም የለም። (መውረዱም) ጌታህ የፈረደው ግዴታ ነው።>>••
ኡለሞች ይላሉ ይህች አንቀፅ ስትወርድ ነብዩና ሰሀቦች አምርረው አለቀሱ ቀጣዪዋ የቁርአን አንቀፅ እስክትወርድ ድረስ
ثُمَّ نُنَجِّى ٱلَّذِينَ ٱتَّقَواْ وَّنَذَرُ ٱلظَّٰلِمِينَ فِيهَا جِثِيًّا
ከዚያም እነዚያን የተጠነቀቁትን እናድናለን። አመጸኞቹንም የተንበረከኩ ኾነው በውስጧ እንተዋቸዋለን።>>••

እያንዳንዳችን በጀሀነም ጀርባ ላይ በተዘረጋው ሲራጥ ላይ እናልፋለን።
ታድያ ይህንን ድልድይ ለመቅዘፍ እሚያስችለን ስራስ ይኑረን ይሆን!???

👣👣 ተጓዦቹ👣👣
••<<የምእመናን ሁኔታ በሲራጥ ላይ>>••

🌹አሏሁ ሱ.ወ አማኞቹ በሲራጥ ላይ የሚኖራቸውን አህዋል እንዲህ ሲል ገልፆልናል፤

🍂يَوۡمَ تَرَى ٱلۡمُؤۡمِنِينَ وَٱلۡمُؤۡمِنَٰتِ يَسۡعَىٰ نُورُهُم بَيۡنَ أَيۡدِيهِمۡ وَبِأَيۡمَٰنِهِم بُشۡرَىٰكُمُ ٱلۡيَوۡمَ جَنَّٰتٞ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَاۚ ذَٰلِكَ هُوَ ٱلۡفَوۡزُ ٱلۡعَظِيمُ
ምእመናንንና ምእምናትን በስተፊቶቻቸው፣ በቀኞቻቸውም ብርሃናቸው የሚሮጥ ሲኾን በምታያቸው ቀን (ምንዳ አልላቸው)። ዛሬ ብስራታችሁ በውስጦቻቸው ዘውታሪዎች ስትኾኑ ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈስሱባቸው ገነቶች ናቸው (ይባላሉ)። ይህ እርሱ ታላቁ ዕድል ነው።>>••

ይህንን ብርሀንን ያገኙ ሙእሚኖች የሚኖራቸውንም ሁኔታ በሌላ አንቀፅ እንዲህ ይለናል።
🍂يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ تُوبُوٓاْ إِلَى ٱللَّهِ تَوۡبَةٗ نَّصُوحًا عَسَىٰ رَبُّكُمۡ أَن يُكَفِّرَ عَنكُمۡ سَيِّـَٔاتِكُمۡ وَيُدۡخِلَكُمۡ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ يَوۡمَ لَا يُخۡزِي ٱللَّهُ ٱلنَّبِيَّ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مَعَهُۥۖ نُورُهُمۡ يَسۡعَىٰ بَيۡنَ أَيۡدِيهِمۡ وَبِأَيۡمَٰنِهِمۡ يَقُولُونَ رَبَّنَآ أَتۡمِمۡ لَنَا نُورَنَا وَٱغۡفِرۡ لَنَآۖ إِنَّكَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ
እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ንጹሕ የኾነችን ጸጸት በመጸጸት ወደ አላህ ተመለሱ። ጌታችሁ ከእናንተ ኀጢኣቶቻችሁን ሊሰርይላችሁ ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውንም ገነቶች ሊያስገባችሁ ይከጀላልና። አላህ ነቢዩን፣ እነዚያንም ከእርሱ ጋር ያመኑትን በማያሳፍርበት ቀን ብርሃናቸው በፊቶቻቸውና በቀኞቻቸው የሚሮጥ ሲኾን «ጌታችን ሆይ! ብርሃናችንን ሙላልን፣ ለእኛ ምሕረትም አድርግልን፣ አንተ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነህና» ይላሉ።>>••

🎈በዚህም የቁርአን አንቀፅ አሏህ የቂያማ እለት እውነተኛ አማኞችን በመልካ ስራቸው ልብ ብርሀንን እንደሚሠጣቸው ነግሮናል።
አብዱሏህ ኢብን መስኡድም
<<በስተፊቶቻቸው የሚሮጥሲሆን>>የሚለውን ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል<<በስራቸው ልክ ሲራጡ ላይ ያልፋሉ፤ለከፊሎቻቸው የተሰጣቸው ብርሀን ስፋቱ እንደተራራ ነው፤የከፊሌቹ እንደ ዘንባባ ዛፍ ፣የከፊሎቹ እንደ ቆመ ሰው ከሁሉም አነስተኛው ሰው ብርሀኑ በአውራ ጣቱ ላይ የሚደረግለት ነው እሱም ብርሀኑ ሲበራለት ወደ ፊት ይሄዳል ሲጠፋበት ደግሞ ይቆማል፤፤

📉ለመሆኑ ብርሀናቸው በተራራ ከተመሰለላቸው ጎራ ለመሆን እሚያበቃ ስንቅን ሰንቀን ይሆን
ከአውራ ጣቱም መሆናንችን እንጃ!!

ወንድሜዋ አሏህ እኔንም አንተንም ከእነርሱ ያድርገን እና የሙእሚኖች ሁኔታ ሲራጥ ላይ ይሄንን ይመስላል(በትንሹ)።
የመናፍቃን ሁኔታስ⁉️

✍️ይቀጥላል ቢአውኒላህ

👣👣 ተጓዦቹ 👣👣

<<ሙናፊቆች በሲራጥ ላይ>>

አሏህ ሱ.ወ የሙናፊቆችንን ሁኔታ በሲራጥ ላይአስመልክቶ የሚከተለውን ብሎናል

يَوۡمَ يَقُولُ ٱلۡمُنَٰفِقُونَ وَٱلۡمُنَٰفِقَٰتُ لِلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱنظُرُونَا نَقۡتَبِسۡ مِن نُّورِكُمۡ قِيلَ ٱرۡجِعُواْ وَرَآءَكُمۡ فَٱلۡتَمِسُواْ نُورٗا فَضُرِبَ بَيۡنَهُم بِسُورٖ لَّهُۥ بَابُۢ بَاطِنُهُۥ فِيهِ ٱلرَّحۡمَةُ وَظَٰهِرُهُۥ مِن قِبَلِهِ ٱلۡعَذَابُ
መናፍቃንና መናፍቃት ለእነዚያ ለአመኑት «ተመልከቱን፤ ከብርሃናችሁ እናበራለንና» የሚሉበትን ቀን (አስታውስ)። «ወደ ኋላችሁ ተመለሱ። ብርሃንንም ፈልጉ» ይባላሉ። ግቢው በውስጡ ችሮታ (ገነት) ያለበት ውጭውም ከበኩሉ ስቃይ (እሳት) ያለበት የኾነ (ደጃፍ ባለው አጥር)።>>••

<ወደ ሃላቹ ተመለሱ ብርሀንንም ፈልጉ ይባላሉ>ዋደ ብርሀን ማከፋፈያው ያመራሉ ምንም እሚያገኙት ነገር አይኔርም ዳግም ወደ ሙእሚኖቹ ሲመለሱ በር ያለው አጥርን በመሀከላቸው ተሰርቶ ያገኛሉ፤
እውስጡ ገነት ደጁ(ውጪው)ደግሞ እሳት!!!
እንዲህም ይባላሉ
•<<ዛሬም ከናንተ ቤዛ አይወሰድም ከነዚያ ከካዱትም መኖሪያችሁ እሳት ናት እርሷ ተገቢያችሁ ናት፤ምን ትከፋም መመለሻ(ይላቸዋል)።>>
ያኔማ እዱንያ ላይ ስቁንቁን የነበረው ሁላ የምድርን ወርቅ ሙሉ ሰጥቶ እራሱን ነሳ ማውጣትን እናት እና አባቱንም ቤዛ እድርጓ ነፃ መውጣትን ይሻል!!ግና ተቀባይነት የለውማ!!
በዚያ ቀን የሚከሰቱት አስደንጋጭ ክስተቶችስ....

••<<አብዩ ክስተት>>••
ውዱ ወንድሜ ሆይ.....
የትንሳዬ ለት ሰዎች የታረዙ ና የተከረዙሆነው ወደ ምርመራው ስፍራ እሚወሰዱበትን ክስተት ልብ በለሀል??

ሀቢባችን እንዲህ ይሉናል"የትንሳኤ አለት የታረዙ፣የተከረዙ(ያልተጫመቱ)ና ያልተገረዙ ሆነው ይቀሰቀሳሉ፤"እናታችን አኢሻም ጠየቀቻቸው ያረሱለሏህ ወንዶች ና ሴቶች አንዳቸው ሌላቸውን እያዩ ባንድ ላይ ይቆማሉን??
ነብያችንም ሰ.ዐ.ወ አኢሻ ሆይ ነገሩ እርስ በእርስ ከመተያየትም የጠና ነው።ብለው መለሱላት

ልቦች በፍርሀትና በስጋት ይሞላሉ፤ኡለሞችም እንደሚሉት ሰዎች ለምርመራ ጀባሩ ፊት ሲጓዙ 3 አይነፍትእንቅስቃሴን ያሳያሉ።
።ከፊሎቹ በፍጥነት ጋላቢ ሆነው ይሄዳሉ፤እነርሱም የጀነት ጓዶች ናቸው
።በዝግመትም እሚሄዱ አሉ፤እነኚህ አምልኳቸውን ያጓደሉ ናቸው
።በፊታቸውእየተደፉ እሚወሰዱም አሉ፤እነኚህ መመለሻቸው ጀሀነም ናት!!
ይህንንም ታላቅ ክስተት አላህ ሱ.ወ በቁርአኑ ላይ ገልፆልናል

🌺وَأَشۡرَقَتِ ٱلۡأَرۡضُ بِنُورِ رَبِّهَا وَوُضِعَ ٱلۡكِتَٰبُ وَجِاْيٓءَ بِٱلنَّبِيِّـۧنَ وَٱلشُّهَدَآءِ وَقُضِيَ بَيۡنَهُم بِٱلۡحَقِّ وَهُمۡ لَا يُظۡلَمُونَ
ምድርም በጌታዋ ብርሃን ታበራለች። መጽሐፉም ይቅቀረባል። ነቢያቱና ምስክሮቹም ይመጣሉ። በመካከላቸውም በእውነት ይፈረዳል። እነርሱም አይበደሉም።>>••
🌹وَوُفِّيَتۡ كُلُّ نَفۡسٖ مَّا عَمِلَتۡ وَهُوَ أَعۡلَمُ بِمَا يَفۡعَلُونَ
ነፍስም ሁሉ የሠራችውን ሥራ ትሞላለች፤ (ትሰፈራለች)። እርሱም የሚሠሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነው።

🌹قِيلَ ٱدۡخُلُوٓاْ أَبۡوَٰبَ جَهَنَّمَ خَٰلِدِينَ فِيهَاۖ فَبِئۡسَ مَثۡوَى ٱلۡمُتَكَبِّرِينَ
«የገሀነምን ደጃፎች በውስጧ ዘውታሪዎች ስትኾኑ ግቡ። የትዕቢተኞችም መኖሪያ ምን ትከፋ!» ይባላሉ።

አላህ ሱ.ወ እኔንም እናምተንም ከዚህ ዕለት ጭንቀት ና ፍርሀት ነጃ ቡሎን ትካዜ ከሌለባቸው የጀነት ጓዶች ያድርገን።አሚንን

👣👣ተጓዦቹ👣👣

••<<ጀነት እና ፀጋዎቿ>>•

🌹ውዱ ወንድሜ...
የጀነት ፀጋዎች በቃላት የማይገለፁና በሀሳብ ፈፅሞ የማይደረሱ ናቸው።
አንድ ቀን ሰሀቦች ጀነት ውስጥ ስላለው ፀጋ ሀቢቡን ሰ.ዐ.ወ ይጠትቋቸዋል፤ረሱልም ሰለሏሁ አለይሂ ወሰለም ይመልሱላቸዋል፦ጠጠሮቹ ሉልና ያቁት ናቸው።አፈሩም ዛእፈራን ነው፤የገቧት ይጠቃቀማሉ ፀጋ አይከዳቸውም፤ልብሶቻቸው አያልቁም ወጣትነታቸውም አይከዳቸውም በእርሷም ውስጥ ዘውታሪና የማይሞቱ ሲሆኑ፣ሞትም እርም ትሆንባቸዋለች!!

ህንፃዎቿና መኖሪያዎቿ፦ለአማኞች ምቹ የሆኑ ውብ መኖሪያዎች አሏት።አላህም (ሱ.ወ) እንዲህ ይለናል
🌺لَٰكِنِ ٱلَّذِينَ ٱتَّقَوْا۟ رَبَّهُمْ لَهُمْ غُرَفٌ مِّن فَوْقِهَا غُرَفٌ مَّبْنِيَّةٌ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَٰرُ ۖ وَعْدَ ٱللَّهِ ۖ لَا يُخْلِفُ ٱللَّهُ ٱلْمِيعَادَ
ግን እነዚያ ጌታቸውን የፈሩ ለእነርሱ ከበላያቸው የታነጹ ሰገነቶች ያሏቸው ሰገነቶች ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው የኾኑ አልሏቸው። (ይህንን) አላህ ቃል ገባላቸው። አላህ ቃሉን አያፈርስም።

ኢብን ከሲር(አላህ ይዘንላቸውና)እንዲህ ብሏል፤፦<<ልዕልናው የላቀው እና ክብሩ የገነነው አሏህ ደስታን የተጎናፀፉት ሰዎች ጀነት ውስጥ ሰገነቶች እንዳሏቸው ነግሮናል።እነዚህ ሰገነቶች እነርሱም አንዱ ከአንዱ የተነባበሩ ሲሆኑ በክእለትና በጥበብ የተገነቡ ህንፃዎች ናቸው።ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ግንባታውን ሲገልፅ እንዲህ ይለናል፦
<<ግንባታቸው ከብርና ከወርቅ ሲሆን ቅባቸው ደግሞ ሚስከል ኢዝፈር ነው።>>

የጀነት ድንኳኖች፦አላህ ስለጀነት ውስጥ ዱንኳኖች እንዲህም ብሎ ይገልፅልናል፦

🌺حُورٌ مَّقْصُورَٰتٌ فِى ٱلْخِيَامِ
በድንኳኖች ውስጥ የተጨጎሉ የዓይኖቻቸው ጥቁረትና ንጣት ደማቅ የኾኑ ናቸው።>>••

ጀነት ውስጥ ከሉል የትሰሩ ድንኳኖች አሉ።የእያንዳንዱ ስፋት 60 ማይል ሲሆን ከስፋቱ የተነሳ በየ ማዕዘኑ አማኞች እሚዘዋወሩባቸው የማይታዩ ቤተሰቦች አሉ።
የጀነት ዛፎችና ፍራፍሬዎች፦አላህ ጀነት ውስጥ ብዙ አይነት ፍራፍሬ ና ዛፎች እንዳሉም ነግሮናል
የወይን ፍሬ የሩማን ዛፍ እንዲሁም ዘንባባዎች ሲጠቀሱ ቁርቁራ እና የሙዝም ተክልም ይገኙበታል•

🌺إِنَّ لِلْمُتَّقِينَ مَفَازًا
ለጥንቁቆቹ መዳኛ ስፍራ አልላቸው።
حَدَآئِقَ وَأَعْنَٰبًا
አትክልቶችና ወይኖችም።>>•

••<<🌺وَأَصْحَٰبُ ٱلْيَمِينِ مَآ أَصْحَٰبُ ٱلْيَمِينِ
የቀኝም ጓዶች ምንኛ (የከበሩ) የቀኝ ጓዶች!
فِى سِدْرٍ مَّخْضُودٍ
በተቀፈቀፈ (እሾህ በሌለው) ቁርቁራ ውስጥ ናቸው።>>••

በቁርአን አያዎች ስለ ጀነት ፀጋና ኒዕማዎች ለጉድ ተዘርዝሯል
በምንድነው ታድያ የጀነት ባለቤት ለመሆን እምንከጅለው!??

የጀነት ሰገነቶች በመናፈሻዎቿ ውስጥ ያሉትን ኒዕማ አላሁ ሱ.ወ እንዲህ ይለናል፦
••<<فِيهَا سُرُرٌ مَّرْفُوعَةٌ💚
በውስጧ ከፍ የተደረጉ አልጋዎች አልሉ።

وَأَكْوَابٌ مَّوْضُوعَةٌ
በተርታ የተኖሩ ብርጭቆዎችም።

وَنَمَارِقُ مَصْفُوفَةٌ
የተደረደሩ መከዳዎችም።
وَزَرَابِيُّ مَبْثُوثَةٌ
የተነጠፉ ስጋጃዎችም (አልሉ)።>>••

✍️አደራህን ግን ወንድሜ ፀጋዎቿን በምናብህ ለመሳል እንዳትሞክር ብትሞክርም እንኳ ልኳን አታገኝምና፤
በሰሂህ ቡኻሪና ሙስሊም ላይ እንደተዘገበው
የጀነት ፀጋዎች በማንም አዕምሮ ላይ ውል የማይሉ ናቸው።

ታድያስ መንገደኛው ወንድሜ ለራህማኑ እራስህን አስገዛ ከጌታህም መሀርታን ከጅል ቅጣቱንም ፍራ!!
ውዷ እህቴ ከሀቢቢ ጋር መጓራበትን ከነ ኸዲጃህ አኢሻህና ፋጢማ የምዕመናን እናት ከሆኑት ጋር አብሮነትን አትፈልጊምን!?
ታድያ!!ፍላጎት ብቻ ሆነሽ አትቅሪያ ወድ ጀሊሉ ተዋደቂ እንቁዎቹን አርአያ አድርጊ ለማንም ተላላ ትችትና ወቀሳ አታጎብድጂ!!
ምክንያቱም ጀነት እንጂ ዱንያ አይደለምና አላማሽ!!

👣👣 ተጓዦቹ👣👣

<<ጀነት እርም የሆነባቸው!!>>

✍️ውዱ ወንድሜ አላሁ ሱ.ወ ጀነትን እርም ስላደረገባቸው ጭፍራዎች ሰምተሀልን??
እንግዲያውስ ና ተከተኝ..

ሀቢባችን(ሰ.ዐ.ወ) ጀነትን ስለተከለከሉ ሶስት አይነት ሰዎች ነግረውናል[የኸምር ሱሰኛ፣ ወላጆቹን አዛ እሚያደርግ ና ደዩስ(በቤተሰቡ/በባለቤቱ ምንም አይነት ቅናቻ የሌለው)

አቡኹረይራ ረ.ዐ በዘገቡት ሀዲስ ነብዩ ሰዐ ወ የሚከተለውን ተናግረዋል፦
፡የኸምር (መጠጥ) ሱሰኛ
፡የአራጣ(ወለድ)ገንዘብ ተጠቃሚ
፡የየቲሞችን ገንዘብ ያለ ሀቅ የሚበላና
ወላጆቹን እሚያስቸግር!!!

✍️በሁለቱም ሀዲሶች ውስጥ የተጠቀሰ አንድ አንገብጋቢ ጉዳይ አለ
የወላጆች ሀቅ!! ወላሂ ለክብደቱ ማሳያ ይበቃዋል አላህ ከራሱ ሀቅ ለጥቆ ማምጣቱ
ስለ ወላጆች ሀቅ ስናወሳ ሁላችንም የምናውቀው ሀዲስን ላስታውስ
(ጀነት በእናት እግር ስር ናት) ኡኽታ ነቃ በይ ወንድሜ አስተውል እናትህን ተኳርፈህ፣ሀቋን አጉድፈህ የራህማን ፊት ለመለመን ትደፍራለህን!!
ስለ ወላጆች ሀቅ ባልደረቀ ብእር እናነሳዋለን ኢንሻ አሏህ

ረሱሉ ሰለሏሁ አለይሂ ወሰለም እንዱህ ብለዋል ሁለት አይነት ሰዎች ይመጣሉ የጀሀነም ጓዶች የሆኑ

*የላም ጭራ የሚመስሉ አለንጋዎችን ይዘው ሰዎችን እሚገርፉ
*ለብሰው እንዳለበሱ ተዘናግተው(የደካማ ወንዶችን ልብ)የሚያዛናጉ ፀጉራቸው ልክ እንደ ግመል ሻኛ የተዘናበለ ሲሆን እነኝህ ሴቶች ጀነትን አይገቧትም ሽታዋንም አይቋደሷትም!!
ኡኽታ!! ተመከሪበት!!

👣👣 ተጓዦቹ👣👣

<<እሳትና ስቃይዋ!!>>

አላሁ (ሱ.ወ)እሳትን በላቀው መፅሀፉ ቅዱስ ቁርአኑ ውስጥ ጠቅሷታል።ስለ አሸድነቷም ገልፆልናል

🌹لَهُم مِّن جَهَنَّمَ مِهَادٌ وَمِن فَوْقِهِمْ غَوَاشٍ ۚ وَكَذَٰلِكَ نَجْزِى ٱلظَّٰلِمِينَ
ለእነርሱ ከገሀነም እሳት (በሥራቸው) ምንጣፍ ከበላያቸውም (የእሳት) መሸፈኛዎች አሏቸው። እንደዚሁም በደለኞችን እንቀጣለን።>>••

<<ያገኘችውን ሁሉ አትተውም አታስቀርምም።>>
ይህ ማለት ስጋቸውን የደም ስሮቻቸውን ነርቮቻቸውን እና ቆዳቸውን ትበላለች (ታቃጥላለች) ሆኖም ግን አይሞቱም ቆዳቸው በተቃጠለ ቁጥር ሌላን ቆዳ ይቀየርላቸዋል!!!

ሙተፈቅ አለይህ በሆነ ዘገባ ረሱል ሰ.ዐ.ወ እንዲህ ብለዋል፤ይህች የምታቀጣጥሉዋት እሳታችሁ የጀሀነም እሳት አንድ ሰባተኛ ናት!!(ሠሀቦችም)በአላህ ይሁንብን ሙቀቷ እንደኛው ቢሆን በቂ ነበር አሉ።ነቢዩም እሷ (ጀሀነም) በስልሳ ዘጠኝ ጊዜ እንድትበልጣት ተደርጎዋል እያንዳንዱም ክፍል ሙቀቱ እንደሷ ነው"

በመሆኑም ሙስሊሙ ወንድሜ ሆይ ከእሳት ተጠንቀቅ።በውስጧ ያሉትንም ሙቀትና ሀሩርነቷን አስታውስ፤እጅግ ከባድ የሆነ ቅዝቃዜዋን ዘቁምን አስታውስ!! እነዚያ ብርቱ እና ጨካኝ የሆኑትን ጠባቂዎቿን አትርሳ።አስታውስ ልክ እንደተጓዥ መድራሻህን እስብ አስተንትንም።በጀሀነም ውስጥ ነዋሪዎቿ ሲጣሩ፣እገዛን ሲጠይቁ ሲጯጯሁ፣ከቅጣቱ ብርቱነት ጥፋትን ሲመኙ አመድ አዋራ መሆንን ሲናፍቁ!!
ፊቶቻቸው ከወንጀሎቻቸው ብዛት ሲጠቁር እግሮቻቸው ከአንገቶቻቸው ሲጠፈሩ ከሁሉ ጥጋጥጎችና ሸለቆዎች ከቅጣት መደራረብ የተነሳ ሲያለቅሱ እና ሲጯጯሁ ብለውም ሲጣሩ"ማሊክ ሆይ ብርቱውን ቅጣት መሸከም አልቻልንም!! ማሊክ ሆይ ቆዳችን ቀልጦዋል!!ማሊክ ሆይ ከእንዲህ አይነቱ ኑሮ አለመኖር ይሻለናል ማሊክ ሆይ ጌታህ ይፍረድልን ማሊክ ሆይ ከዚህ አውጣን ዳግመኛ አንመለስም..."የጀሀነም ጠባቂው የሆነው ማሊክም ከዘመናት በሃላ መልስ ይመልስላቸዋል!!
"እናንት በርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ናችሁ!!"

አስብ ተጓዡ ሆይ አስተንትኚማ እህቴዋ በዱንያ ላይ ሰጥመን ጊዜያው ደስታን ስናሳድ ሞት የመጣን እንደሆን የኃሊት መፀፀታችን አይቀሬ ነው!!

ውዱ ወንድሜ ሆይ፦ እስቲ እራስህን ጠይቅ አፈረጠምኩት የምትለው ሰውነትህ እሳትን መቋቋም ይችላልን!? አይደለም እሳትን አርጩሜም አይቋቋም (አይደል)ታድያ ለ ዚህች ጅስምህ ስሜትህን እየተከተልክ ለምን ልትቋቋመው ወደማትችለው ቅጣት ትነዳታለህ!!
ውዷ እህቴ፦ አይምሰልሽ ውብት ና ዝናሽ ማማር ማስጠላትሽ ጌታሽ ዘንድ ሚዛን የሚደፋ!! ይልቅ ልብሽን አስውቢ ምግባርሽን ሞሽሪ ውስጥሽ ሲስተካከል ውጫዊው ጀሰድሽም በኢማን ያበራል በኑር ይሸፈናል ። አደራ የወንድን እይታ ለመሳብ ብለሽ የጌታሽን ቁጣ ሸምተሽ እንዳትመጪ!!!

👣👣 ተጓዦቹ👣👣

•• <<ራስን ምርመራ>>••

🍂ብልህና አስተዋይ ሰው ነገ ጀባሩ ፊት ከመመርመሩ በፊት እዱንያ ላይ እራሡን ይመረምራል!!
ኡመር ፋሩቁ (ረ.ዐ) እንዳሉት "አላህ ዘንድ ከመገምገምህ በፊት እራስህን ገምግም"
ግን እንዴት እራሴን ልመርምር??
ቢአውኒሏህ ቀጣዩቹን መጠይቆች እራስህን በራስህ እንድትጠይቀው እንካ ብዬሀለሁ
•5ቱንም ሰላቶች በጀመዐ መስጂድ ተጥደህ ትሰግዳቸዋለህን??
•ዛሬ ከቁርአን የቀራሀው ምዕራፍ አለን?
•ሞትን አኼራን በዛሬዋ ቀንህ አስታውሰሀልን ወይንስ በብልጭልጭ አረንጓዴዋ ተ ወጥረህ ዘነጋሀት?
•በዛሬው ቀንህ ለፈፀምካቸው ወንጀሎች ማራኝ ረቢ ብለሀልን!?
•አደራ ቡሀላ ነገ ከነገ ወድያ እያልክ ለተውበት ቀጠሮ እንዳጥል ሞት ከጫማ ክርህ በላይ ቅርብህ ነውና!!!
•ዛሬ የመፀወትከው ሰደቃ(ትንሽም ብትሆን) አለህን፤
ቆይ ትንሽ ልሰብስብ እህህ ገና ቤት መች ገዛሁ ገናም አላገባሁ ገና...እያልክ ለስስታምነትህ ምክንያትን አትደርድር ገና ብለህ ገና ሳትጨርስ ሞትህ ከተፍ ሊል ይችላልና!!
ትንሽም ብትሆን መመፅወትን ልመድ ብዙ ሲኖርህ ብዙውን ለመስጠት አትቸገርምና።
•ወላጆችህን በጎ ውለህላቸዋልን!!
•ጌታህን በብዛት አውስተሀልን!?
•በውዳችን ሀብብ ላይስ ሰለዋትን አውርደሀልን!?
•የሰዎችን ሀቅ መልሰሀልን!?
•የምትበላው፣የምትጠጣው፣ና የምትለብሰው ልብስ ምንጭን ከሀላል መሆኑንብ አረጋግጠሀልን!?
•ከመጥፎ ከልክለህ በጥሩ አዘሀልን!?
•ጌታህን ፈርተህ አንብተሀልን!?
•••ጥፍጥናን ቆራጭ የሆነችዋን ሞት አስታውስ•••

ለሁሉም ጥያቄዎች መልስ ስጣቸው፤ያሉትን ጉድለቶች ለማስተካከል ጣር ወንጀል ላይ ከመውደቅ ተጠንቀቅ፤የወንጀልህን ትብሽነት ሳይሆን የወነጀልከውን ጌታ ትልቅነትን አስተውል!!

👣👣ተጓዦቹ👣👣

••<<የስሜት ጎዳና ፍፃሜ>>••

✍ውዷ እህቴ፦ስሜትን በመከተል ደስታን ለማግኘት
ከሚዳክሩት መሀል እንዳትሆኚ፤ይልቅ ስሜታቸውን ተከትለው የወደፊታቸውን በዱንያም በአኼራ ያበላሹትን እያየሽ ተመከሪ።

ውዱ ወንድሜ፦አይምሰልህ ወጣትነትህ ከሞት የሚታደግህ ቆም በል አስብም ወደ አንድ አዛውንት ጠጋ ብለህ ስለ ወጣትነት ጊዜያቸው ያወጉህ ዘንድ ጠይቃቸው!!"አይይ ያኔማ ጉልበት እያለኝ ጤነኛ ሆኜ ሳልሰግድ ያሳለፍኳቸው ቀናቶች ቁጭቴ..." ለነሱ ከንፈር መምጠጥህን አቁመህ የነገው አንተው መሆንህን እወቅ ! እድሜ ካለህ !!

የዱንያ ፀጋ አይሸንግልህ ፀጋዋ በአንድ የጀሀነም ንክርያ የሚረሳ ነውና!!
ረሱል ሰ.ዐ. ወ እንዲህ ብለውናል

<<በዱንያ ላይ ከነበሩት ሁሉ የበለጠ ኒዕማ የነበረው እና እሳት ከተፃፈባቸው ውስጥ አንዱን የቂያማ ዕለት በማምጣት አንዴ እሳት ውስጥ ነከር ተደርጎ ይወጣና "የአደም ልጅ ሆይ በዱንያ ውስጥ ጥሩ ነገር አጋጥሞህ ያውቃልን!?" ፀጋስ አልፎብህ ያውቃልን!?ይባላል!!
"በጌታዬ ይሁንብኝ በፍፁም ኸይር የሚባል ነገር አልፎብኝ አያውቅም"

ዋ አጀባ ❗በአንድ የጀሀነም ንክርያ የምትዘነጋ ምን የቀለለች ብትሆን ነው!!

🌺 ሩሱሉ ሠለላሁ አለይሁ ወሰለም
ዱንያ አላህ ዘንድ የትንኝ ክንፍ ያህል እንኳ ቦታ እንደሌላት ነግረውናል።

🍁አየህ አይደል ዱንያ ምንም እንደሆነች
ይልቅ በዱንያ ነዋሪ ለአኼራው ሰሪ ሆነህ
የመንገዳኛን ምርኩዝ ተቅዋህን ሰንቀህ
ኢላሂ ካንተው ነኝ ላንተም ወዳንተም ነኝ
በዚህች አጭር ሀገር እኔ እንግዳ ነኝ

ሁሉም ሲቦርቁ ሲደሰቱ ላፍታ
በዱናያም ድሎት ሲሉም እንፍታታ
ኢላሂ እንዳረሳህ አርገሀኛል ላፍታ

መንገዳኛ ሆኜ እኔ አንተኑ ብያለሁ
ኢላሂ በእዝነትህ መሀርታን እላለሁ!!!

'ጌታህን አብዝተህ ለምነው መሀርታንም ጠይቀው።'

  በመጨረሻም ትእዛዛቱን የምንከተል ውዴታውን የምናገኝ ቅኑን መንገድ የምንመራ፤ሌሎችንም የምንመራ፤ከመጥፎ ምንከለክል፤በጥሩው ምናበስር፤ለረበና የምንኖር፤ ለርሱ ትእዛ የምናድር፤ስንኖርም በዚህ ምድር፤እንደተጓዥ መንገደኛ፤ባይተዋሮች ሆነን እኛ፤እንለያይ በዚህ ምድር
እስክንገናኝ በዛ ማዕሸር ፤

ሰላት ሰላም በውዱ በአህመዱ
በኹልቁ አደድ ልክ አውርድም ሰመዱ

ሰላም እንደ ጎርፉ
ሶላት እንዳረፋ
ያጥለቅልቆትም ደርሶ ሐቢቢ ሙስጦፋ

#ተቋጨ